የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 34
ADDIS ABABA - 6[th] June, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፬/፲፱፻፺፪ ዓ.ም

ለነጆ–መንዲ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........... ገጽ ፩ሺ፫፻፲፫

## CONTENTS

Proclamation No. 204/2000

OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Nejo-Mendi Road Project Ratification Proclamation ............................ Page 1313

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፬/፲፱፻፺፪

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለነጆ–መንዲ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፱ ሚሊዮን ፭ መቶ ሺህ (ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፱ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለነጆ–መንዲ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፬/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 204/ 2000

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of USD 9,500,000 (nine million five hundred thousand United States Dollars) for financing the Nejo-Mendi Road Project, was signed in Addis Ababa on the 21[st] day of December, 1999;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 6[th] day of June, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for financing the Nejo-Mendi Road Project Ratification Proclamation No. 204/2000."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፱ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር ፯፻፸፮ፒ የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፱ ሚሊዮን ፭ መቶ ሺ (ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 776 P signed in Addis Ababa on the 21st day of December, 1999, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of USD 9,500,000 (nine million five hundred thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of June, 2000.

Done at Addis Ababa, this 6th day of June, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE